# ወያኔ ፣በብሔር ብሔረሰቦች መነገድ ይብቃህ
# ኢትዮጰያ የሁሉም እኩል አገር ትሆናለች

በአለም ላይ በየጊዜው በርካታ የታሪክ አጋጣሚዎች ይፈጠራሉ ፣ አንዳንዶች የተፈጠረውን አጋጣሚ በሚገባ በመጠቀም ለአገርና ለሕዝብ የሚጠቅም ታላላቅ ሥራዎችን ይሠራሉ ፣ ሌሎች በአንፃሩ የተፈጠረውን አጋጣሚ በማባከን አገርንና ሕዝብን የሚጎዳ ታሪካዊ በደል ይፈጽማሉ፣ ወያኔ በኢትዮጵያ በተፈጠረው አጋጣሚ ለመግንስት ሥልጣን በቅተሀል ፣የተፈጠረውን አጋጣሚ ለምንና እንዴት እየተጠቀምክበት እንደሆነ መመልከት ጠቃሚ ነው።

የኢትዮጵያሕዝብ በገዥዎች ይደርስበት የነበረውን በደል ለማስወገድ አመፅና ትግል አካሂዷል ሁሉም ትግሎች ብሶት የወለዳቸው እንደመሆናቸው በነፃነት ፣በዲሞክራሲና ፍትህ ጥያቄዎች ላይ አተኩረዋል ፣የወያኔም የብሶት ትግል በእነዚሁ ጥያቄዎች ላይ ያተኩራል  የሚል ግምት ነበር።

በኢትዮጵያ ረጅም የመንግስት ታሪክ ሥልጣን ይያዝ የነበረው በጦርነት ሲሆን ፣ አቅምና ጉልበት የነበረው ሥልጣን ሲነጥቅ፣ተሸናፊው ይወገዳል፣የሁሉም ገዥዎች ዓላማ ግን የኢትዮጵያን አንድነት ፣ዳርድንበርና ሉዓላዊነት ጠብቆና አስከብሮ መግዛት ነበር።

በጦርነት የመንግስት ሥልጣን ሽግግር ሂደት ዘመነ መሣፍንት አክትሞ ማዕከላዊ መንግስት ብቅ አለ ፣እየተጠናከረም መጣ፣ ለዚህ  ውጤት ቴዎድሮስ፣ ዮሐንስ ፣ምኒልክና ኃይለሥላሴ በዋናነት ይጠቀሳሉ፣ ሁሉም የኢትዮጵያን አንድነት፣ ዳርድንበርና ሉዓላዊነት ለመጠበቀና ለማስከበር  የማያወላውልና የፀና አቋም ነበራቸው፣ በተግባርም አሳይተዋል ቴዎድሮስ በመቅደላ፣ ዮሐንስ በመተማ ፣ የሕይወት መስዋዕት ከፍለዋል፣ ምኒልክ በአድዋ አኩሪ ድል አስመዝግበዋል፣ ኃይለስላሴ የጣሊያን ወረራ ለመቀልበስ ታላቅ ሚና ተጫውተዋል፣ ደርግም የሱማሌን ወረራ በአኩሪ ድል አክሽፏል።

ወያኔ ጫካ እያለ ግልጽ የሆነ ዓላማ አያመለከትም ነበር፣ እያፈተለኩ ከሚወጡት መረጃዎች መካከል የትግራይ ሪፑብሊክን መመስረት ፣ ትግራይ ትግሪኝ ሪፑብሊክን መመስረት፣ ኢትዮጵያን የሁሉም ዕኩል አገር ማድረግ፣ኢትዮጵያን  ማፈራረስ የሚሉት ይገኙበታል።

ወያኔ አዲስ አበባ ከመግበቱ በፊት የኦሮሞ ሕዝብን ቀልብ ለመሳብ ኦነግን አግባባ (አታለለ ማለቱ ይሻላል )፣መልሶ ኦነግን ለመምታት ኦሮሞ ምርኮኞችን አሰባስቦ ኦህዴድን ጠፈጠፈ፣ ለአማራው ኢህዲን ፣ለደቡብ ሕዝቦች ደህዴንን አዘጋጀ፣  ከኦነግ ውጪ ከሶስቱ ጋር ኢህአዴግ የሚል ድርጅት ፈጠረ፣ በእነዚህ ታጅቦ ፣በሻብያ ተደግፎ አዲስ አበባ ገብቶ የሽግግር መንግስት በማቋቋም ሥልጣን ያዘ።ወያኔ ሜዳውም  ፈረሱም እንደተመቻቸለት ሲረዳ፣ ወያኔ ኢትዮጵያን ይገዛል፣ ኢትዮጵያ የምትባል አገር የምትኖረውወያኔ እስከገዛ ድረስ ብቻ ነው፣ አለበለዚያ ግን ትፈራርሳለች የሚለውን ደብቆ ያቆየውን ታላቁን ሤራውን ብቅ አደረገ፣ ዕውን ለማድረግም የተለያዩ እርምጃዎችን ወሰደ።

## 1. ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ማፈራረስ

በወያኔ አስተሳሰብ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት  ለወያኔ የሥልጣን ሕልም ሥጋት ናቸው፣ የኢትዮጵያና  የኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብ አቀንቃኞች አማራና ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ናቸው፣ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማፈራረስ በቅድሚያ አማራንና ኦርቶዶክስ ሃይማኖትን ማዳከም የወያኔ ልዩ ትኩረት ሆነ።

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ከወያኔ በፊትለምዕራባውያንም ስጋት ነበሩ ፣ ምኒልክ ዘመናዊ መሳሪያ  እስከአፍንጫው ታጥቆ የመጣውን የጣሊያን ወራሪ ኃይል አድዋ ላይ አሸንፈው ከፍተኛ ውርደት አደረሱበት፣ በአንድ ኋላ ቀር አፍሪካዊ አገር በጣሊያን ላይ የደረሰው ውርደት

የምዕራብያውያንም ውርደት ተደርጎ ተወሰደ፣ እንዲቆም ካልተደረገ የምዕራብያውያን ክብርና ጥቅም የበለጠ እንደሚጎዳ ግንዛቤ ተወስዶ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የማፈራረሱ ዕቅድ ተፀነሰ ፣አልተሳካላቸውም እንጂ ተግባራዊ ለማድረግ በሚሲዮናዊያን ፣ በተመራማሪዎች ፣ በዲኘሎማቶችና በሌሎች ዘዴዎች ከፍተኛ ጥረትአድርገዋል፡፡

ወያኔ በቅድሚያ ሥጋት ናቸውባላቸውበአማራና በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ላይ ዘመቻውን ከፈተ፣ ዘመቻውን ፍጻሜ እስከሚያደርስ ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችን በብሔረሰቦች ፌዴሬሽን ልጓም ይዞ የሚቆጣጠርበትን ሥልት ዘረጋ ፣ ዘመቻው አስተማማኝ ደረጃ ሲደርስለት ሌሎቹን እንደስጋት ደረጃቸው ቅደምተከተል ተራ በተራ ከፖለቲካው ውጭ ለማድረግ ተዘጋጀ፡፡

ወያኔ አማራን መምታት የጀመረውበከፈተው ቅስም ሰባሪና አዋራጅ የስነልቦና ጦርነት ነው፡፡ ቀጥሎም በወተር፣ በአረካ፣በበደኖ ፣በባሌና በሌሎች ቦታዎች ጨፈጨፈ፣ ከነሕይወቱም ወደገደል ወረወረ፣ የአማራን ቁጥር ለመቀነስ የአማራ ሴቶች እንዳይወልዱ የሚያመክን መርፌ በመውጋት አሳፋሪ ዘረኛ ተግባር ፈፀመ፡፡

በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ውስጥ ረጅም እጁን አስገብቶ አደረጃጀቱን፣ አመራሩንና አሰራሩን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠረ፣ በውስጡም የወያኔ ካድሬዎችን ሰገሰገ ፣ሌሎቹን በማባረር ዘረኝነትን አስፋፋበት ፣የኦርቶዶክስ ሃይማኖትም የወያኔ ፍላጎት ማስፈፀሚያ ሆነ፣ስብሐት ነጋም ከዚህ ተነስቶ አማራና ኦርቶዶክስ ሃይማኖት አለቀላቸውተመቱ አለ፡፡

ወያኔ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ፈጽሞ ማፈራረስ አይቻልህም፣ ኢትዮጵያዊነት የብዙ ሺህ ዘመናት ታሪክ ያለው፣ በኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ ሰርፆ የገባ፣ በኢትዮጵያዊያን ደምና አጥንት የለመለመ፣ የኢትዮጵያዊያን ታሪክ ፣ባህልና ማንነት መገለጫ ነው፣ይህን ጥልቀትና ግዝፈት ያለውን አስተሳሰብ የጎልማሳ እድሜ እንኳን በሌለው የወያኔ አስተሳሰብ እተካለሁ ብለህ ማሰብህ ቅዠት ነው፣ቱርኮች፣ ግብጾች፣ድርቡሾች/ መሐዲስቶችና ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ሲወሩ ድባቅ እየመታ የመለሳቸው ኢትዮጵያዊነት ነው፣ እነአብርሐም ደቦጭ በአዲስ አበባ ፣ አብዲሳ አጋ በሮም ፣የፈጸሙት ታሪካዊ ጀግንነት ኢትዮጵያዊነት ነው፣በኢትዮጵያ በየቦታውለነፃነት፣ ለዲሞክራሲና ለፍትህ የተደረጉና በመደረግ ላይ ያሉ ትግሎች ኢትዮጵያዊነት ናቸው፣ የሳውዲ ዐረብያ መንግስት በኢትዮጵያዊያን ላይ ያደረሰውን ግፍና ሰቆቃ በመቃወም ኢትዮጵያዊያን ሃይማኖት ፣ ዘር፣ ፆታና ፖለቲካ ሳይገድባቸው በየሳውዲዐረብያ ኢምባሲዎች በመሰብሰብ ቁጣቸውን አሰምተዋል፣ድርጊቱን አውግዘዋል ፣ ወገኖቻቸውን ደግፈዋል፣ አጽናንተዋል፣ የታየው ተቆርቋሪነት፣አጋርነትና ደራሽነት ኢትዮጵያዊነት ነውበአጭሩ ኢትዮጵያዊነት ለኢትዮጵያ አንድነት፣ ዳርድንበርና ሉዓላዊነት ፣ እንዲሁም ለኢትዮጵያ ህዝቦች ክብርና ነፃነት የሚደረግ ትግልና የሚከፈል መስዋዕትነት ነው፣ ይህን ተጋፍቶ የሚመጣ ሁሉ ኢትዮጵያዊነት ይፋለመዋል፡፡ኢትዮጵያዊነት በቅኝ ግዛት ወድቀው ለነበሩ የነፃነት፣ የአንድነት፣የሉአላዊነት፣የጥንካሬ፣የአላማ ጽናትና የአይበገሬነት ተምሳሌት ስለነበረ፣ለአፍሪካ የነፃነት ታጋዮች በተለይም ለአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ(ANC)የትግል መነሻ፣መደራጃና መታገያ ፍልስፍና ሆነ፡፡

በአንፃሩ ወያኔነት ዘረኝነት ፣ ጠባብነት ፣ስግብግበነት፣ ከሐዲነትና አፍራሽነት ነው፣ ከሁሉም በፊት ወያኔ፣ ሁሉም ነገር ለወያኔ ብሎ የተነሳ ፣አገራዊና ህዝባዊ አጀንዳ የሌለው አስተሳብ ነው፣ አገርን ፣ታሪክንና ማንነትን የማፈራረስ ተልዕኮ ነው፣ኢትዮጵያዊነትን እያጥላላ የመለስ ዜናዊና የወያኔን ታሪክ የሚኳኩል ነው፣ የአገር ዳርድንበር ለሱዳን ፣ የገበሬ ለም መሬት እየነጠቀ ለውጭ ኩባንያዎች መሸጥ ማለት ነው፣የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያ ህዝቦችን ብሔራዊ ክብር ማስደፈር ማለት ነው፡፡

በአጭሩ ወያኔነት ዘመናዊ አፓርታይድ ስለሆነ የኢትዮጵያን ህዝቦች በዘር በዘር ከልሎ ተለያይተው እንዲኖሩ የማድረግ አስተሣሰብ ነው፣ የዘር፣ የቋንቋ፣ የባህልና የእምነት ልዩነት ኖሮአቸው በአንድነት አብረው እየኖሩ ኢትዮጵያ የጋራ አገራችን ናት፣ ዜግነታችንም ኢትዮጵያዊ ነው ብለው እንዳያስቡ የሚገታ አመለካከት ነው፡፡ ለወያኔ አገሩ፣ ዳርድንበሩ፣ ሉዓለዊነቱ፣ ዜግነቱ ፣ብሔራዊ ክብሩና ማንነቱ ጥቅሙ ብቻ ስለሆነ ወያኔነት የኢትዮጵያን ህዝቦች በዘር

በዘር ክልሎ እየተቆጣጠረ የራሱን የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት የሚያረጋግጥበት ፍልስፍና ነው::

## 2. የትግራይን ህዝብ ለወያኔ አላማ ማሰለፍ

የትግራይ ልጆች የህይወት መስዋዕት የከፈሉት፣ ወያኔ የመንግስት ስልጣን የያዘው ለረጅም ጊዜ ከፖለቲካ የተገለለውን የትግራይ ህዝብ ወደ ክብሩና ተገቢ ቦታዉ ለመመለስ ፣ትግራይን በአጭር ጊዜ ዘመናዊና የዳበረ ኢኮኖሚ ያላት ፣ሰፊና የተደራጀ ማህበራዊ አገልግሎት የተዘረጋበት ክልል ለማድረግ ነው ሲል ወያኔ አናፈሰ፣ ቀጥሎም የወያኔ መንግስት የትግራይ ህዝብ መንግስት ነው፣ ወያኔ ስልጣን ላይ ከሌለ የትግራይ ህዝብ ህልውና አደጋ ላይ ይወድቃል የሚል ማስፈራሪያ አራገበ፣ ይህ እንዳይሆን የትግራይ ህዝብኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ትቶ ወያኔነትን እንዲቀበል የሚል ቅስቀሳ አጧጧፈ ፣ ይህ ሁሉ መሯሯጥ የትግራይን ህዝብ ለአላማው ለማሰለፍ ነው፣ወያኔ የትግራይን ህዝብ ለአላማዬ አሰልፌ እጠቀምበታለሁ የምትለውን ቅዠትህን አቁም ፣አይሳካልህም ምክንያቱም :-

የትግራይ ህዝብና ወያኔ በታሪክ፣ በባሕል፣ በማንነትና በአላማ የተለየዩ ናቸው፣ትግራዊነት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ሲሆን ፣ወያኔነት ግን ፀረ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ነው ኢትዮጵያ ከመቶ ዓመት የዘለለ ታሪክ የላትም፣የታሪኳ መነሻ ከወያኔ ዘመን ጀምሮ መሆን አለበት ብለህ ልብወለድ ስትጽፍ የአባቶችህን ፣ የአያቶችህንና የቅድመ አያቶችህን ታሪክ አታውቀውም ወይም ክደኸዋል ማለት ነው፣የአክሱም ስልጣኔንና የአክሱም ዘመነ መንግስት ለአንተ ለወያኔ ትርጉም የላቸውም፣ ለነገሩማ የአክሱም ሐውልት ለሌላው ምኑ ነውብለህ፣ የአንተን አባባል ልዋስና አዲስ አበባ ለወያኔ ምንህ ሆኖ ነው ሰተት ብለህ ገብተህ ስልጣን የያዝከው::

የትግራይ ህዝብ ልጆቹ የህይወት መስዋዕት መክፈላቸውን ያውቃል ፣በልጆቹም ሞት ያዝናል፣ በአላማቸው ግን ይኮራል፣ ምክንያቱም የትግራይ ልጆች የህይወት መስዋዕት የከፈሉት ወያኔ እንደሚለው የትግራይን ህዝብ ወደ ክብሩና ተገቢ ቦታው ለመመለስ ሳይሆን የትግራይ ህዝብ እንደሚለው መላው የኢትዮጵያን ህዝብ ወደክብሩና ተገቢ ቦታው ለመመለስ ነው::

የትግራይ ህዝብ በደም በታሪክና በባህል ከተሳሰሩት ኢትዮጵያዊያን ወንድሞቹ ጋር ለብዙ ሺህ ዘመናት አብሮ ኖሯል ፣ወደፊትም ይኖራል፣ ሁሉም በጋራ የኢትዮጵያን አንድነት፣ ዳርድንበርና ሉዓላዊነት ጠብቀዋል አስከብረዋል፣ሁሉም ኢትዮጵያዊያን በፈለጉት ክልል በነፃነት ተዘዋውረው ሰርተዋል ፣ኖረዋል፣ ተጋብተዋል ፣ተዋልደዋል፣ በዚህ ሂደት ከተመሰረተውና እየዳበረ ከመጣው ኢትዮጵያዊነት ማንነቱና አካሉ የትግራይን ህዝብ የሚነጥለው አንዳችም ኃይል አይኖርም፣ከኢትዮጵያዊያን ወገኖቼ ጋር አትለያዩኝ አታቆራርጡኝ ብሎ ምክርና ጥያቄ ሲያቀርብ በትግራይ ሽማግሌዎች ላይ የተወሰደውአሳፋሪ እርምጃ የሚረሳ አይደለም ፣ትንሽ ክልል ይዞ ለብቻ መኖር ያለውን ጉዳትና ጥቅም ኤርትራን እንደ ቤተ ሙከራ ወስዶ ማየት ይቻላል::

ወያኔ መረዳት ያቃተህ ከጎንደር ነቅለህ በወሰድከው የኤሌክትሪክ ጀነሬተርና በሌሎች ክልሎች ወረትና ቁሳቁስ ትግራይ እንደማትለማ፣ ከጎንደርና ከወሎ ቦጭቀህ በወሰድካቸውመሬቶች ትግራይ እንደማትሰፋ ነው፣ የትግራይ ህዝብ ሰፊ ክልል ፣ የደለበ ሃብትና ለም መሬት ያላት በደሙና በአጥንቱ የገነባት ኢትዮጵያ የምትባልታሪከዊ አገር አለችው አገሩ ኢትዮጵያ ትልቅ ገበያ ናት ፣ ትልቅ ገበያ በየዘርፉ ግዙፍ ምርት ይሻል ፣የትግራይ ህዝብ የሚፈልገው ልማት ከአገሩ ከኢትዮጵያ መሬት፣ ሀብትና ህዝብ በዕቅድ ተቀናጅቶ የሚመነጨውን ልማትና እድገት ነው::

በታሪክ፣ በባህልና በማንነት ከትግራይ ህዝብ ጋር የማትጣጣም ወያኔ፣ከትግራይ ህዝብ በመወለዴ እኮራለሁ እያልክ ሱዳን ኢትዮጵያን በወረረበት ጊዜ አፄ ዮሐንስን ጨምሮ በርካታ የትግራይ ህዝብ የህይወት መስዋዕት ከፍሎ ያስከበረውን ዳር ድንበር የወያኔ ተቃዋሚዎች በሱዳን እንዳይደራጁና እንዳይንቀሳቀሱ ለማስደረግ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ከነአያቶችህ ደምና አጥንት ለመለማመጫ ለሱዳን ያስረከብከው ወያኔ፣ዛሬ ያስረከብከውን የመለማመጫ መሬት ነገ

ልጆችህ ለማሰመለስ እንደአያቶችህ የህይወት መስዋዕት እንደሚከፍሉ መገንዘብ የተሣነህ ወያኔ ፣ ዓላማችሁ ከኔ ፍላጐት ጋር አይሄድም ያልካቸውን የትግራይ ልጆት በረሃ ጨፍጭፈህ የመጣህ ወያኔ፣ የትግል ዓላማችን ተቀለበሰ ብለው ከድርጅቱ እራሳቸውን አግልለው በሌላ መድረክ (አረና፣ት.ህ.ዲ.ን . . . )እየታገሉ ባሉ ላይ ጥቃት የምታደረስ ወያኔ፣ ትግሬ ሆናችሁ እንደወያኔ ሳይሆን እንዴት እንደ ኢትዮጵያዊ ታስባላችሁ በማለት የምታዋክብ ወያኔ፣ ከአብራክህ የወጡ ልጆችህ ሳይሸማቀቁ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ በኢትዮጵያዊነታቸው ኮርተው እንዳይኖሩና የአንተየወያኔ ዕዳ ከፋይ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን የምታመቻች ወያኔ፣መወለድ ቋንቋ ነውና በየትኛው ታሪክህ፣ ባህልህ፣ ማንነትህና የሞራል ብቃትህ ነው የትግራይን ህዝብ ለዓላማዬ አሰልፌ እጠቀምበታለሁ የምትለው ? እርሳው! ወያኔ ለትግራይ ህዝብ «ላም እሳት ወለደች፣እንዳትልሰው ይፈጃታል እንዳትተወው ልጅ ሆነባት» የሚለውን ሆንከበት::

## 3. የኢትዮጵያ ህዝቦችን በሃይማኖት፣ በጎሳና በክልል መከፋፈል

ወያኔ ሥልጣን እንደያዝክ ጣሊያን እንዳደረገው የኢትዮጵያን ህዝቦች በሃይማኖት፣ በጎሳና በክልል ሸነሸንክ :: የእስልምናና የክርስትናን ሃይማኖቶችን፣ በደንበረና መሬት ይገባኛል ሰበብ ክልሎችንና ጎሳዎችን፣ በዘር አማራንና ሌሎች ብሔረሰቦችን አጋጨህ::በመሰሪ ተንኮልህ ህይወት ጠፋ፣ ንብረት ወደመ መስጊዶችና ቤተክርስቲያኖች ተቃጠሉ ::

በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ላይ ዘር እንዲፃፍ አድርገህ መታወቂያ እያየህ በዩኒቨርሲቲዎች፣ በሞያ ማስልጠኛዎች፣ በኢንባሲዎች፣ በሰራዊቱ፣ በፀጥታና በደህንነቱ እንዲሁም በሌሎች ተቋማት የሌሎች ብሔረሰቦችን አልፎ አልፎ ጣል ጣል እያደረግህ የራስህን በገጠጠ መልኩ ኢትዮጵያ የአንድ ብሔር አገር እስክትመስል ሰገሰግክበት፣ ዘረኝነትን አስፋፋህበት ይህን ያደረክበት ምክንያት ግልጽ ነው ይኸውም ሌሎች ብሔረሰቦች ቅሬታ ሲያሰሙ ፀረ ትግሬነት ነው ብለህ ትግሬዎችን በማሸበር ወደ ወያኔ ጉያ ገብተው እባክህ አድነን እንዲሉህ ተመኝተህ ነው:: የወያኔ ፍላጐት ማንኛውም ፀረ ወያኔ ተቃውሞ ፀረ ትግሬ መስሎ እንዲታይልህ ነው::ትልቁ ስህተትህ ግን አሁን አንተ የምታምሳቸው የኢትዮጵያ ህዝቦች ከአንተ በፊት ለብዙህ ሺህ አመታት አብረው ኖረዋል፣ ደጉንም ክፉንም አሳልፈዋል በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል ገዢዎች እየፈጠሩ ከሚጭኑባቸው ቅራኔ መለስ ያለውን በዲሞክራሲያዊና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ይፈቱታል :: የኢትዮጵያ ህዝቦች ወያኔን ከወያኔ በላይ ያውቁታል ወያኔ ግን ፍላጎቱን እንጂ የኢትዮጵያን ህዝቦች አያውቃቸውም የችግርህም መነሻ በአንተ በኩል የሚታየው የግንዛቤ ማነስ ነው::

በኢትዮጵያ የመንግስት ታሪክ እንደ ወያኔ ያለ ዘረኛ መንግስት ፈጽሞ አይታወቅም:: ወያኔ በዘር ተደራጅቶ፣ ዘረኛ ዕቅድ ነድፎ ከሰማንያ አምስት በላይ ብሔር ብሔረሰቦች ያላትን አገር ኢትዮጵያን በብቸኝነት እየገዛህ ነው:: በአደባባይ ስልጣን የያዝኩት የብሔረሰቦችን ችግር ለመፍታት ነው እያልክ፣ ዘወር ብለህ በሹክሹክታ ለትግራይ ህዝብ ክብርና ጥቅም ነው ትላለህ እውን የብሔረሰቦችን ጭቆና ለመፍታት ከሆነ የመብት ጥያቄ በማቅረባቸው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኦሮሞችን፣ ሲዳማዎችን፣ አኝዋኮችን፣ ሱማሌዎችንና ሌሎችን በእስር ቤት ባላጎርካቸው ነበር ::

አሳፋሪ ድርጊትህ ያሰገኘልህ ጥቅም የለም ምክንያቱም በእስልምናና ክርስትና እምነቶች መካከል ያለውን ፍቅርና ትብብር መስበር አልቻልክም፣ ሁለቱም በጋራ እየታገሉህ ነው፣ በየመድረኩ አንድነታቸውንና አብሮነታቸውን እየገለጹ ነው፣ ብሔረሰቦችን መነጣጠል አልቻልክም፣ ሴራህን ሁሉም ስለተረዳው ከአንተና ከካድሬዎች በቀር ሁሉም ብሔረሰቦች አብረው እየኖሩ ነው::ለሆዳቸው ያደሩልህ ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያውያን ተለይተው እንደማይኖሩ፣ ወያኔም ጥሎአቸው እንደሚፈረጥጥ፣ የወያኔ እዳ ከፋይም እንደሚሆኑ ጠንቅቀው ያውቁታል::ሳይመሽባቸውም ተገቢውን እርምጃ ይወሰዳሉ::

የኢትዮጵያ ህዝቦች ታሪካቸውንና ባህላቸውን ፣ገዢዎች ያደረሱባቸውን ግፍና በደል፣ ብልጣ ብልጥ የፖለቲካ ነጋዴዎች ተቆርቋሪ መስለው ያደረሱባቸውን ሰቆቃ በሚገባ ይረዳሉ::ሁሉም

ብሔረሰቦች ኢትዮጵያ እኩል የጋራ አገራቸው እንድትሆን ፣በነፃነትና በዲሞክራሲ በጋራ አብረው እንዲኖሩ፣ የስልጣን ባለቤት ሆነው ያላንዳች ገደብ በነፃነት ያሻቸውን መምረጥ ይፈልጋሉ።

ወያኔ በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ ታሪካዊ ስህተት እየፈፀምክ ነው፣ አታልዬ ፣አንዱን ከሌላ ጋር አጋጭቼ፣ በጥቅማጥቅም ደልዬ፣ አልተባበር ያለውን አስሬ ፣ገድዬ እገዛለሁ፣ እኖራለሁ የምትለው ጊዜ አልፎበታል።የኢትዮጵያ ህዝቦች ስትመጣ ተቀበሉህ ፣ስትናገር አዳመጡህ፣ ስትሰራ አዩህ፣ ማንነትህን አወቁህ፣ መከሩህ ፣ተቃወሙህ ፣አልሰማሀቸውም ።ከውጭ ተቆርቋሪዎችም ምክር ተለገሰህ።ለምሳሌ ማንዴላ የክፉ ቀን ደራሻችን ኢትዮጵያን ተከፋፍላ ማየት አንፈልግም በማለት ወያኔ እርቅና ሰላም አውርዶ የኢትዮጵያ ህዝቦች ሳይከፋፈሉ በአንድነት ወደ ዲሞክራሲ ሽግግር እንዲያደርጉ ለመለስ ዜናዊ ሃሳብ ቢያቀርብም ሰሚ አላገኘ ም። ዛሬ ሁለቱም የሉም አልፈዋል።የሚታወሱት ግን በተለያየ ሁኔታ ነው። ማንዴላ የነፃነት አርበኛ፣ የሰላምና የእርቅ ሃዋርያ ፣የአንድነት ፣የእኩልነትና የዲሞክራሲ ተምሳሌት ተብሎ ሲታወስ፣ መለስ ደግሞ በአገር አፍራሽንት፣ በብሔራዊ ክብር ደፍጣጭነት፣ በዳር ድንበር ሻጭነት፣ በታሪክ ደምሳሽነት፣ በዘረኝነት፣ በጠባብነትና በፈላጭ ቆራጭነት ይታወሳል።

## 4. የወያኔን የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚና ወታደራዊ አቅም ማጠናከር

ወያኔ ለስልጣንህ ስጋት ናቸው ባልካቸው ላይ ያለርህራሄ እርምጃ ወስደሀል ፣አነግን ሳይውል ሳያድር ከአገር አባረርከው፣ ሌሎችን አሰርክ ገደልክ ደብዛቸውን አጠፋህ፣በ1997 ምርጫ በዝረራ ስትሸነፍ የምርጫውን ውጤት ዘረፍክ ፣ ቅንጅቶችን አሰርክ፣ ከአገርም እንዲባረሩ አደረግህ፣ በ2002 ምርጫ የኢትዮጵያን ህዝብ አንድ ለአምስት ጠርንፈህ ምርጫውን ዘጠና ዘጠኝ በመቶ አሸነፍኩ አልክ ፣ በሰላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን እጅ ከወርች አስረህ አላላውሳቸው አልክ የነፃ ኘሬስ ጋዜጠኞችንናየተቃዋሚፓርቲ አባላትን ፀረ ሽብር ህግ አውጥተህ እስር ቤት አጎርካቸው፣መገናኛ ብዙሐንን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥረህ በዚህ ተግባርህ የፖለቲካ ጉልበተን አሳበጥኩ ብቸኛ የፖለቲካ ተዋንያንም ነኝ አልክ።

አዲስ አበባ እንደገባህ የሌሎች ክልሎችን ሀብት እየሰበሰብክ በጫካ ውስጥ ሳለህየኢትዮጵያን ሀብት ዘርፈህ ወደ አቋቋምከው ምሽግህ ኤፈርት አስገባህ ፣ቀስ በቀስ በትራንስፓርት፣ በኮንስትራክሽን ፣ በባንክ ፣በኮንትሮባንድና በሌሎች ዘርፎች ተሰማርተህ አገሪቱን ቦጠበጥክ በመንግስት ጨረታና በሌሎች ጥቅማጥቅሞች የራስህ ድርጅቶች ብቸኛ ተጠቃሚ አድርገህ፣ ሌሎችን ፈነገልክ ፣ድርጅቶችህ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተበድረው ያልመለሱት ከሁለት ቢሊዮንብር በላይ ገንዘብ ጨምሮ ከላይ በተዘረዘረው ስልት ባከማቸኸው ሀብት ከአገሪቱ ኢኮኖሚ የበለጠ የኢኮኖሚ ኃይል ሆንኩ አልክ።በነገራችን ፣ያንተ የወያኔ ብቻ ሳይሆን የምርጥ አባላትህና ቤተሰቦችህ የኢኮኖሚ ጡንቻ ፈርጥሟል። በአዲስ አበባ እስከ አሁን በሊዝ ከተላለፈው መሬት ሲሦው የተያዘው በአባላትህና በቤተሰቦችህ ነው። እነርሱን ከዚህ ደረጃ ለማድረስ በቅድሚያ በብዙ ሺህ ሜትር ካሬ መሬት በሊዝ ሰጥተህ ቀጥሎም እየሸነሸኑ እንዲሸጡ ፈቅደህ በአንድ ጀንበር ቢጠሯቸው የማይሰሙ ሚኒየነሮች አደረካቸው። እነሱ ሸጠው ሲጠግቡ መሸጥ የሚፈቅደውን መመሪያ አገድከው።

ወያኔ ሁሉንም ነገረ የምትመለከተው በራስህ ባህሪና ስነልቦና ነው፣ በወያኔ አስተሳሰብ በደርግ ስርአት የነበረው የመከለከያ ሰራዊት የደርግ እንጂ የኢትዮጵያ አልነበረም፣ በወያኔ ጊዜ የሚኖረው የመከላከያ ሰራዊት የወያኔ እንጂ የኢትዮጵያ መሆን የለበትም ስለምትል የሰራዊቱ ምልመላ፣ ስልጠና፣አደረጃጀትና አሰራር በወያኔ ፍላጎት ላይ እንዲመሰረት አደረክ፣የወያኔ ሰራዊት ህልውና ወያኔ እስካለ እንጂ ከዚያ ውጭ ህልውና እንደማይኖረው ለማስፈራራት የደርግ ሰራዊት ነው የምትለውን አፈራረስክ ፣ በተንክ፣ የመንግድ ዳር ለማኝም አደረካቸው፣ በተመሳሳይ ፍልስፍና የፖሊስ ሰራዊቱን የፀጥታና የደህንነት ኃይልን እንደ ወያኔ መከላከያ ሰራዊት አደራጀህ፣ በውስጡም ከአዛዥ እስከ ተራ አባል የወያኔ አባላትን ሰገሰግክበት።

ከላይ በተመለከተው ስልት ወያኔ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ወታደራዊ ጡንቻህን አፈረጠምኩ አልክ ዛሬ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሀይል ሳይሆን የወያኔ፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሳይሆን የወያኔ፣

የኢትዮጵያ የፖሊስ ሰራዊት ሳይሆን የወያኔ፣ የኢትዮጵያ የፀጥታና የደህንነት ኃይል ሳይሆን የወያኔ፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት ሳይሆን የወያኔ፣ወደሚባልበት ደረጃ አድርሼዋለሁ በማለት በትዕቢት ትኩራራለህ፣ ማን ይደፍረኛል፣ እኔ ነኝ ያለ ይሞክረኝ እያልክ ትደነፋለህ፣ ትዕቢትና ዕብሪት የውድቀት ግማሽ መንገድ ናቸው፣ ወያኔ አዲስ አበባ ሰተት ብለህ ገብተህ ስልጣን ላይ ፊጥ ያልከው ህዝቡ ባደረገልህ ትብብርና ድጋፍ ነው፣ይህን ክደህ በጀግንነቲ ነው የምትል ከሆነ በምስራቅ አፍሪካ አቻ የለውም ይባል የነበረው የደርግ ሰራዊት እንዴት እንደፈረሰና እንደተነነ ከወያኔ ይበልጥ የሚያውቀው የለም፣ብልህ ከሌላ ፣ ሞኝ ግን ከራሱ ይማራል እንዲሉወያኔከደርግ ትምህርት መውሰድ ካልቻልክ እጣ ፋንታህ ያው እንደ ደርግ ነው።

### ማጠቃለያ

በዓለም ላይ ዛሬ ህጋዊ ህልውና ያላቸው አገሮች ባለብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ይሁኑም አይሁኑም ዛሬ ከደረሱበት ደረጃ ለመድረስ ብዙ ውጣ ውረድ አሳልፈዋል። ዛሬ አብረው በሚኖሩት ህዝቦች መካከል ግጭትና ጦርነት ፣ እርቅና ሰላም ተፈራርቀዋል፣ አገራቸውምይጠብ ይሰፋ ነበር፣ ያለፈ ታሪካቸውን በአግባቡ መዝግበው ዘግተዋል፣ ስለወደፊቱ የጋራ ህይወታቸው ተወያይተው በነፃነት፣ በዲሞክራሲና በእኩልነት ለመኖር ተስማምተው አብረው እየኖሩ ነው፣ይህን በማድረጋቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ መልማትና ማደግ ችለዋል።

ኢትዮጵያም ይህን መንገድ ብትከተል ችግሯይፈታል፣ልማቷና እድገቷም ይፋጠናል የኢትዮጵያ ችግር ከትውልድ ወደ ትውልድ ተንከባሏል ፣ትውልድም አላስፈላጊ ዋጋ ከፍሏል፣ ችግሩ ሊወገድ የሚችልበት በርካታ አጋጣሚዎች ተፈጥረው ነበር ግን የተጠቀመባቸው የለም፣ ፍላጐት ካለ አሁንም እድሉ አለ፣ ይህ ትውልድ ችግሩ በእኔ ይብቃ ይፈታ ማለት ከቻለ ለሚቀጥለው ትውልድ ሰላማዊና ለሁሉም እኩል የምትሆን አገር ማስረከብ ይችላል ፣ይህን ማድረግ ከተቻለ ለትውልድ የተበረከተ ታላቅና ታሪካዊ ስጦታ ይሆናል፣ዋናውና ትልቁ ቁምነገር አገሪዊና ህዝባዊ አጀንዳ ሰንቆ ፣የፖለቲካብስለት ጨምሮ፣ የግልም ሆነ የቡድን የስልጣን ፍላጐት ገትቶ መወያየት ከተቻለ ስምምነት መድረስ ይቻላል፣

ችግሩ፣ ችግሩ ሳይሆን ችግሩን ለመፍታትየሚንቀሳቀሱት ሰዎች አመለካከትና ቁርጠኝነትነው፣ ግልጽነት፣ መልካምነት፣ ቀናነትና እርቆ ተመልካችነት ካለ በብዙ አገሮች እንደሆነውበኢትዮጵያም ችግሩ በቀላሉ ይፈታል፣በአንፃሩ ግልጽነት ከጎደለ ፣ድብቅ ፍላጎት ካለ፣ ወደ ግል ወይም ወደቡድን ፍላጎት ካዘነበለ እርቆ አስተዋይነት ከጠፋ ችግሩ ይወሳሰባል መግባባትም ይከብዳል፣ ኃይለ ሥላሴ በውስጥም በውጭም የተመቻቸ ሁኔታ እየነበራቸው በግል ክብርና ዝና ተጠምደው ዕድሉ አመለጣቸው፣ ደርግም ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም እያለ የአስራ ሰባት ዓመት ቅዠቱ ቅዠት ሆኖ ቀረ፣ወያኔ ቂም በቀል ቋጥሮ፣ ዘረኝነትንና ጠባብነትን አዝሎ፣ ስግብግብነትንና እራስ ወዳድነትን አስቀድሞ በኢትዮጵያ ችግር ላይ ነዳጅ አርከፈከፈበት ።

ኃይለስላሴ በዝናቸው እያሰቡ፣ ደርግ በትከሻው እያሰበ፣ ወያኔ በምላሱና በሆዱ እያሰበ፣ ሁሉም ከህሊናቸው እርቀው አገርንና ህዝብን ጎዱ በደሉ፣ ኃይለ ሥላሴ አጉል አሟሟትና ውርደት ደረሰባቸው፣ደርግ ተፈረካከሰ እንደጉም በነነ፣ የወያኔ ቁንጮ መለስ ዜናዊ አገርን አዋርዶና እራሱም ተዋርዶ፣ውርሴና ቅርሴ የሚለውንየኳኳለውንና የአሽሞነሞነውን ታሪክ ለትዝብት ትቶ ሄደ የመለስ ዜናዊ ፍጡር ወያኔ ወደ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የመመለስ እድል አለህ፣ ወያኔነት አጥፊህ ነው የኢትዮጵያ ህዝብ ሆደ ሰፊ ስለሆነ ይቅር ይልሀል።

ኢትዮጵያ ለዘላለም በክብር ትኖራለች
ደመቀ በሪሁን